**አስክ ኔትወርክ** የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል ኃይለኛ መገለጥ እና ትግበራዎች ያለበት የጥሞና ልምምድ
አቤቱ፥ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።መዝሙር 19፡14
/ASK NETWORKMeditating on the Word of GodA devotional practice with powerful implications and applications/

# Meditating in the Word of God

## in Amharic

**አስክ ኔትወርክ** በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ነው። ለእግዚአብሔር የውጊያ ትጥቅ የሚገልፀው የኤፌሶን 6 ምንባብ በዚህ ቃል ተደምድሟል፡ *የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ የመዳን ራስ ቁር* (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:17-18) የክርስቶስ ልብ ስላላቸው ክርስቲያን የሚገልፅ ነው። *የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው* ማለት የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ምክር ነው። *በመንፈስ መጸለይ* ማለት ለምልጃችን መማር፣ መታጠቅ እና መብቃት ነው። በአስክ ኔትወርክ ውስጥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች እንደ መሆናችን ቃሉን ከፍተን በመንፈስ ቅዱስ ተደግፈን የእርሱ ልብ እንዳለን እናምናለን። ይህ ቡክሌት የአግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል ለሚደረግ የግል የጥሞና ጊዜ ልምምድ መመሪያ እንዲሆን የታሰበ ነው ፤ እንዴት የማሰላሰያ ጊዜያችሁን እንደምታጎለብቱ እና በመለመን ውስጥ እንዴት ያሰላሰላችሁትን ነገር እንደምትጠቀሙበት ተግባራዊ ምክሮችን ይሰጣል።

## የእግዚአብሔርን ቃል የማሰላሰል የጥሞና ልምምድ

አንድ ሰው ጥሞና ሕይወቱ ውስጥ በግል ቃሉን የማሰላሰል ልምድን ካዳበረ የእግዚአብሔርን ድምፅ በቃሉ ውስጥ መስማትን ይለምዳል። ደንካን ካምቤል ቃሉን ማንበብ ጥሩ እንደሆነ አስተምሯል፤ ነገር ግን ቃሉ በእኛ ማለፉ የበለጠ ወሳኝ ነው ፤ ይሄ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ለማሰላሰል ጊዜ በመውሰድ የሚመጣ ነው። ይሄ የነፍስ የሚያብላላበት ቦታ በማለት ይገለፃል ፤ ይሄ ቃሉ እንዴት የእኛ አካል እንደሆነ ያስተምረናል። አንዱ ይሄን ለመረዳት የሚረዳን እጃችንን በምናባችን መሳል ነው። ጣቶቻችሁ የእግዚአብሔርን ቃል የምንማርባቸውን መንገዶች እንደሚወክሉ አስቡ፤ ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ትምህርት፣ በቃል መያዝ እና መዘመር ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስን በአራቶቹ ጣቶች ሚዛናዊ ማድረግ ትችላላችሁ። ነገር ግን ለመያዝ ግን አውራ ጣታችሁ ያስፈልጋል። ነገር ግን ጣቶቹ እና አውራ ጣት አንድ ላይ ሲሆኑ በቀላሉ ማንም ሊውስደው በማይችልበት ደረጃ የእግዚአብሔርን ቃል ይዛችሁታል።

**መጽሐፍ ቅዱስን የማሰላሰል ሌላው ትርጉም << የእግዚአብሔርን ቃል ማመንዠግ ፣ ማስተዋል እና ማንፀባረቅ>>>** ጂም ፓከር እንዲህ ይላል ፡ *ማሰላሰል ወደ አእምሮ የመመለስ ፣ ደጋግሞ የማሰብ ፣ በዚያ ላይ መቆየት እና አንድ ሰው የሚያውቀውን የእግዚአብሔርን ሥራ፣ ዓላማ እና ተስፋ በራስ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ነው። በማስተዋል በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ በእግዚአብሔር ዓይን ስር ፣ በእግዚአብሔር እርዳታ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ የቅዱስ ሃሳብ ተግባር ነው። ዓላማው አንድን ሰው የእግዚአብሔርን አእምሮአዊ እና መንፈሳዊ ራዕይ ማጥራት እና በአንድ ሰው አእምሮ እና ልብ ላይ ሙሉ እና ትክክለኛ ተፅዕኖ እንዲፈጥር መፍቀድ ነው።*

*ኤ. ደብሊው. ቶዘር የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማሰላሰልን እንዲህ ይገልፀዋል፡ እግዚአብሔርን ተረጋግተን መጠበቅ ወሳኝ ነገር ነው። በተጨማሪም በተለይ መጽሐፍ ቅዱሳችን ከፊታችን ተዘርግቶ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻችንን መሆናች ምርጥ ነገር ነው። ከዚያ ከፈቀድን እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ሲናገረን መስማት እን ምራለን። ለአንድ ሰው እድገቱ ይህን ይመስላል፡ መ መሪያ በአትክልት ቦታ አንድ ሕልውና በእግር እየሄደ ያለ የሚመስል ድምፅ እንሰማለን። ከዚያ የሚሰማ ግን ከግልፅነት የራቀ ድምፅ እንሰማለን። ከዚያ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል መግለጥ ሲ ምር የደስታ ጊዜ ይሆናል እና ያ ድምፅ ብቻ የነበረው፣ ሲሻሻል ደግሞ ንግግር የሚመስለው እንደ ውድ ጓደኛ ንግግር የሚገባ፣ ሞቅ ያለ እና ቅርብ ንግግር ይሆናል።*

*መጽሐፍ ቅዱስን ማሰላሰል እንደ ልምድ የሚተገብሩ ሰዎች ከጌታ ጋር የጠለቀ እና ሽልማት ያለው ልምምድ እንዳላቸው ግልፅ ነው። በአስክ ኔትወርክ ውስጥ ለመለመን ለመዘጋ ት እና በልመና ውስጥ በመንፈስ ለመመራት ወደ ጌታ መቅረብ፣ በቃሉ እና በመንፈሱ ድምፁን መስማት መሻታችን ነው።*

አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሲያሰላስል አእምሮአቸው ስለ እግዚአብሔር በማሰብ ይሞላል። ይሄ የአንድን አእምሮ ሃሳቦች ከማስወገድ ነገር ግን በማይካድ ሁኔታ ራስ-ተኮር ከሆነ ተነጥቆ ማሰላሰል በጣም የተለየ ነው።

## ስለማሰላሰል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጠቃሻዎቹ

በእግዚአብሔር ቃል (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ላይ ማሰላሰል ወይም ማሰላሰል ተግባር የሚሉትን ቃላት በግልፅ የተጠቀመው 21 ጊዜ ብቻ ነው፡

* ኢያሱ 1፡8 ይዘህ፤ ብቻ አንተ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ የሰጠህን ትእዛዝ ሁሉ በጥንቃቄ ጠብቅ፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።
* መዝሙር1፡1-2 በክፉዎች ምክር የማይሄድ፣ በኀጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣ በፌዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ፣ሰው ብፁዕ ነው። ነገር ግን ደስ የሚሰኘው በእግዚአብሔር ሕግ ነው፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል።
* መዝሙር 48፡9 አምላክ ሆይ፤ በቤተ መቅደስህ ውስጥ ሆነን፣ ምሕረትህን እናስባለን።
* መዝሙር 49፡3 አፌ የጥበብን ቃል ይናገራል፤ የልቤም ሐሳብ ማስተዋልን ይሰጣል።
* መዝሙር 104፡34 እኔ በእግዚአብሔር ደስ እንደሚለኝ፣የልቤ ሐሳብ እርሱን ደስ ያሰኘው።
* መዝሙረ 119፡97-99 97አቤቱ፤ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ! ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ። ትእዛዛትህ ምንጊዜም ስለማይለዩኝ፣ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረጉኝ። ምስክርነትህን አሰላስላለሁና፣ ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የላቀ አስተዋይ ልብ አገኘሁ።

ነገር ግን እግዚአብሔርን የመጠበቅ፣ በሕልውና ውስጥ የማደር፣ ከእርሱ ጋር በቅርበት ሕብረት የማድረግ፣ እርሱን እና ቃሉን የማሰብ፣ መሰብሰብ፣ መደሰት እና የመሳሰሉት ጽንሰ ሃሳቦች በሙሉ የእግዚብሔር ቃል ውስጥ ተሰፍተዋል። የዚህ ጥቂት ምሳሌዎች እና ስዕሎች እነሆ፡

* መናን እንደ ፍላጎት መጠን በየቀኑ መሰብሰብ. ዘፀአት 16፤
* መኃ.2:3 በዱር እንዳለ እንኮይ፥ እንዲሁ ውዴ በልጆች መካከል ነው። ከጥላው በታች እጅግ ወድጄ ተቀመጥሁ፥ ፍሬውም በጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው። 4 ወደ ወይን ጠጅም ቤት አገባኝ፥ በእኔ ላይ ያለው ዓላማውም ፍቅር ነው።
* ሕዝ. 3:1-3 እርሱም፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ ያገኘኸውን ብላ ይህን መጽሐፍ ብላ፥ ሄደህም ለእስራኤል ቤት ተናገር አለኝ።2 አፌንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጐረሰኝ። 3 እርሱም፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ አፍህ ይብላ፥ በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ። እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ።
* ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እን ራውን አንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤ 31 ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።ሉቃ. 24:30-32
* እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል። ራእ.3:20

ከዚህ በላይ ተጨማሪ ምሳሌዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ ራሳችሁ በመመልከት ልትደሰቱ ትችላላችሁ። በእርግጥ የእግዚብሔርን ቃል ማሰላሰል ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ታረጋግጣላችሁ : :

## የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ማሰላሰል ይቻላል

እዚህ ጋር ዓላማው ከእግዚአብሔር ቃል ለመቀበል የሚረዱትን አንዳንድ እርምጃዎች ለመጠቆም ነው። በምንም መንገድ እነዚህ መመሪያዎች እንደ ሕግ ልንከተላቸው የሚገቡ ትዕዛዝ አይደሉም፤ነገር ግን ጌታ እንደሚመራችሁ ተከተሏቸወ እና የእግዚአብሔርን ቃል የምታሰላስሉበት ጊዜ በጣም የጎለበት እና ሽልማት ያለው ይሆናል።

የምታሰላስሉበት ጊዜ የግል ከሆነና እና የመደበኛ የጥሞና ልምምዳችሁ አካል ከሆነ ወደ ቃሉ በአ ንዳ የመምጣታችሁ ሁኔታ እምብዛም አይሆንም፤ ነገር ግን ወደ ቃሉ ስትመጡ እግዚአብሔር ለመናገር የሚፈልገውን ነገር ለመስማት ባለ ጥበቃ ውስጥ ሆናችሁ ነው። ትንሽ ልዩነቱ ወደ ቃሉ ስለተወሰነ ርዕስ ለመጸለይ ስትመጡ መንፈስ ቅዱስ ለጸሎት ትኩረታችሁ ልትተገበሩት የምትችሉትን የእግዚአብሔር ቃል ምንባብ እንድትመርጡ እንዲረዳችሁ በማመን ነው። ለምሳሌ ኤፌሶን ስለ ክርስቶስ ሙሽራ ብዙ ያካባተ ክፍል ነው፤ ስለዚህ አንድ ሰው እንዚህ ምዕራፎች ለቤተ ክርስትያን መጸለይ የሚችልባቸውን ሁሉንም ዓይነት አስደናቂ እውነቶች እንደሚገልጡለት ይጠብቃል። እንደውም ኢየሱስ እራሱ ቃሉን ለቤተ ክርስቲያን እንደሚያውል ተገልጧለል፡ ኤፌ.5፡26-27 በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። ስለዚህ ስናሰላስል በመ  መሪያ በማሰላሰል ጊዜ ያገኘነውን ቃል በመተግበር የየጸሎት ርዕሱ ያለማቋረጥ አእምሮአችን ውስጥ እንዲሁም በልመናችን ውስጥ ይቀመጣል።

## የተጠቆሙ መመሪያዎቹ፡

* ጸጥታን ፈልጉ፡ በእርግጥ ጸጥ ያለ ቦታ ላይ መሆን ይረዳል ነገር ግን ጌታ ማንኛውንም ዓይነት ሃሳባችን የሚሰርቁ ነገሮች ከአእምሮአችን እንዲያስወግድ መጸለይ ወሳኝ ነው። ከዓለም፣ ከሥጋ እና ከዲያቢሎስ የሆኑ ረባሽ ሃሳቦችን እንዲወገድ ጸልዩ እና አእምሮአችሁን ከመንፈስ ቅዱስ እንዲቀበል ቀድሱት።
* በአምልኮ ምሩ፡ ይህ ለእግዚአብሔርን ማንነት እውቅና የመስጠት (ከታች ያሉትን የእግዚአብሔርን ስሞች ተመልከቱ) ወይም ከሌሎች ጋር የመዘመር ያክል ቀላል ነው። የተለመዱ መዝሙሮችን ወይም ዜማዎችን መዘመርን ይጨምራል ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ወይም ከመዝሙረ ዳዊት አንድ ምንባብ ወስዳችሁ መንፈስ ቅዱስ እንደመራችሁ በነፃነት መዘመር ትችላላችሁ። ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርግልን ልንለምነው ስላለው እግዚአብሔር ማንነት ማወጅ ውስጥ ኃይል አለ። ደግሞም ልባችንን ለመለመን ያዘጋጃል እና እምነታችንን ያነቃቃል።
* ለመለመን ትኩረት አድርጌ፡ ብቻችሁንም ወይም ከሌሎች ጋር ስትፀልዩ በአእምሮአችሁ የጸሎት ርዕስ ከሌለ ጌታ ስለምን እንድትለምኑ እንደሚፈልግ በማስተዋል ጠይቁት። ስታሰላስሉ ያንን ትኩረት በአእምሮእችሁ ይዛችሁ ቃሉን እዚያ ላይ ታውስተውላላችሁ።
* የእግዚአብሔር ቃል ምንባብ፡ ምንባብ ምረጡ፤ የአንድ ጥቅስ ያክል ሊያጥር ይችላል ነገር ግን ከአንድ ምዕራፍ መርዘም የለበትም። አውዱን ተመልከቱ ፤ ይህ መረዳታችሁን ያግዛል። ቀስ ብላችሁ አንብቡት ፤ካስፈለግ ደጋግሙት። መንፈስ ቅዱስን ጌታ ሊያሳያችሁ የፈለገውን ፣ ምን ዓይነት መረዳት እንዲኖራችሁ እንደፈለገ እንዲጠቁማችሁ ጠይቁት። ትኩረታችሁን የሚስብ አንድ ቃል፣ ሃሳብ፣ጥቅስ፣ ግሶቹ፣ የአንድ ሰው ስም ወይም የመሳሰሉትን ልታገኙ ትችላላችሁ። ቆም በሉና እዚያ አንድ ነገር ላይ አተኩሩ። ራሳችሁን በልዩ ሁኔታ እንዲያስብ ፍቀዱለት። ከዚያ ጋር የሚገናኙ ሌሎች ቃላት ሊመጡ ይችላሉ። ስታሰላስሉት ሁሉም ዓይነት አስደናቂ ሃሳቦች፣ መረዳቶች እና መገለጦች ወደ አእምሮአችሁ ይመጣሉ። ጌታ እየተናገረ እንደሆነ ማመን አለባችሁ እና ለጸሎታችሁ ትኩረት ለምን እንደሚጠቅም ማየት ት  ምራላችሁ። ይህንን ላልተለማመደ ሰው ለማስረዳት ከባድ ነው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተለመዱ ምንባቦች ጭምር አይታችሁ የማታቁትን ነገር በእርግጥ ታያላችሁ።

* የምታሰላስሉትን ነገር መዝግቡት፡ ከቻላችሁ ያሰባችሁት ሁሉ ብትፅፉት በጣም ጠቃሚ ሆኖ ልታገኙት ትችላላችሁ። ይሄ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡ ሃሳባችሁን ሥርዓት እንድታስይዙት ይጠቅማል ፤ በተቀበላችሁት መጸለይ ይቀላል እና እግዚአብሔር እንዴት ጸሎታችሁን እንደመለሰ የምትቆጣጠሩበት መዝገብ ይኖራችኋል።
* ያሰላሰልነውን ነገር መረዳት፡ ማሰላሰላችሁን እንደጨረሳችሁ እንደተሰማችሁ እና ለመጸለይ የተወሰኑ ነገሮች ካገኛችሁ መጸለይ መ መር ትችላላችሁ። ከሌሎች ጋር እየጸለያችሁ ከሆነ ሁላችሁም በአጭሩ መረዳታችሁን ለሌሎች ማካፈል አለባችሁ። እንዴት የሁሉም ሰው ማሰላሰል ተጣጥሞ ሙሉ ስዕል እንደሚሰጣችሁ ስትመለከቱ ትገረማላችሁ።.
* ያሰላሰልነውን ነገር መተግበር፡ በማሰላሰል ያገኛችኋቸው እውነቶች በመ  መሪያ ለእናንተ የግል ጥቅም ይኖረዋል። አንዴ ያንን መረዳት ከተቀበላችሁ ለየትኛውም የጥያቄ የትኩረት አቅጣጫችሁ ለማዋል ዝግጁ ናችሁ። እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ ስልት የመቀበልን ዓይነት ነው። የተቀበላችሁትን በስልጣን ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዳሳያችሁ እና ልመናችሁን እንደሚመልስ በመተማመን ጸልዩ።

ምስጋና፡ የማሰላሰል ጊዜያችሁን ደምድሙ እና እንደ ትኩስ እን  ራ ከቃሉ አዲስ ነገሮች እንድታዩ ስለፈቀደላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት። በቸር ታማኝነቱ ልመናችሁን ስለሚመልስ አመስግኑት።

## መጽሐፍ ቅዱስን የማሰላሰል ጥቅሞቹ

የእግዚአብሔር ቃል ማሰላሰል በጣም ብዙ ጥቅሞች አሉት። ምን ያህል በረከቶች እንዳሉት ለመረዳት አንዱ መንገድ ብዙዎቹ የተዘረዘሩበትን መዝሙር 119 ማንበብ ነው። ያዕቆብ 1፡21 እንዲህ ይላል፡- ዕብ. 4፡12 የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤ ይህ ከሁሉም የሚበልጠው ትልቅ ጥቅም ግን በቃሉ እግዚአብሔርን የበለጠ ማወቃችን ነው እና ከእርሱ ጋር ሁሌ የሚጨምር ቅርበት ያለወ ግኑኝነት መ  መራችን ነው።

## በቃሉ መለመን

የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።መዝሙር119፡130
ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል ብርሃን እና መገለጥ እንደሚያመጣ ያረጋግጣል። እግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ ማሰለሰላችንን ሥርዓት እንዲያስዝልን በመፍቀድ ስንጠብቅ ራሳችንን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመጸለይ ዝግጁ ሆኖ እናገኘዋለን። ቃሉን መልሶ ወደራሱ ለመጸለይ ይሄ እርግጠኛ መንገድ ነው። ኢሳ.55፡11 እግዚአብሔር እንዲህ እንደሚል ያውጃል፡- ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።

ቃሉን በጥልቀት በመረዳት መጸለይ የበለጠ በኢላማ መሆን ይችላል። አስከ ኔትወርክ በሁሉም ተግባራቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን መከተል የሚፈልገው ለዚህ ነው፤ ነገር ግን የሚጸልየው በእርግጥ የሚመሰረተው ከእግዚአብሔር በወጣው ቃል ነው። መዝሙር 29 ይህን ይመሰክራል፡ የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ፥ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ።(2)

## ካሌሎቹ መማር

የእግዚአብሔርን ቃል ከተዘገበውን መልሰው የተናገሩ ሰዎች በቀጥተኛ ጥያቄም ሆነ በተዘዋዋሪ እንሆ፡-

* ዳዊት- 2ሳሙ.22
* ዮናስ-ዮናስ 2
* ጴጥሮስ- የሐዋ.ስራ 2
* ጳውሎስ- ሮሜ 9
* ኢየሱስ- ማቴ.27

አስከ ኔታወርክ በዚህ በብዙ እና ኃይለኛ ታሪክ ይቀጠል።

...receive from Him anything we ask, because we obey

## የእግዚአብሔር ስሞቹ

መዝሙረ ዳዊት 138፥2 ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ ስምህንም አመሰግናለሁ፥ በሁሉ ላይ ቅዱስ ስምህን ከፍ ከፍ አድርገሃልና። ይህ ቡክሌት የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ቃል መሆኑን ለማሳየት ፈልጓል። ዕብ.4፥12 እንዲህ ይገልጸዋል፡ የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ የእግዚአብሔርን እውነት ቃሉን በማሰላሰል ስንፈልግ የእግዚአብሔርን ባህሪ አንርሳ፣ እርሱም የልመና ታማኝ መላሽ መሆኑን ነው። በእግዚአብሔር ቃል የመ  መሪያ ገፆች ላይ ባህሪውን ለመግለጥ የተጠቀማቸውን ስሞች ከታች ተዘርዝረዋል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ የተለያዩ ስሞች እና መግለጫዎች አሉት። የትኞቹንም ለማወጅ አታመንቱ እና በልመናችሁ እንደዚሁ ጥሩት።

ያህዌህ ፀባኦት/ Yehovah Tzevaot 'הוהי תואבצ / ፡- የጭፍሮች አምላክ 1 ሳሙ.17፡45
ያህዌህ ኤልየን / Yehovah Elyon 'הוהי ןוילע /፡- ልዑል እግዚአብሔር መዝሙር 7፡17
ያህዌህ ሮኢ/ Yehovah Ro'I 'הוהי יער /፡- እግዚአብሔር እረኛ ነው መዝሙር 23፡1
ያህዌህ ይርኤ/ Yehovah Yireh 'הוהי הארי /፡ እግዚአብሔር አቅራቢ ነው ዘፍ.22፡14
ያህዌህ ንሲ/ Yehovah Nissi 'הוהי יסנ /፡- እግዚአብሔር ዓላማዬ ነው ዘፀ.17፡15
ያህዌህ ሻሎም/ Yehovah Shalom הוה םולש /፡- እግዚአብሔር ሰላም ነው መሳ.6፡24
ያህዌህ ሻማህ/ Yehovah Shamah 'הוהי המש /፡- እግዚአብሔር በዚያ አለ ሕዝ.48፡35
ያህዌህ ጽድቀኑ/ Yehovah Tzidkenu 'הוהי ונקדצ /፡- እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ኤር. 23፡6
ያህዌህ መቀደሽ-ቺም/ Yehovah Mekadesh-chem 'הוהי םכשדקמ /፡- እግዚአብሔር ይቀድሰኛል ዘሌ.20፡8
ያህዌህ ሮፓ-ቻ / Yehovah Ropha-cha 'הוהי ךאפרר /እግዚአብሔር ፈዋሽ ነው ዘፀ.15፡26
ኤሎሂም/ Elohim םיהולא /፡- ዘፍ.1፡1
ኤል ኤልሮኢ እስራኤል/ El Elohei Yisrael לא יהולא לארשי / - እግዚአብሔር ፣ የእስራኤል አምላክ ዘፍ.33፡20
አዶናይ/ Adonai ינדא .፡- ዘፍ.15፡2
ኤልሻዳይ/ El Shaddai לא ידש .፡- ሁሉን ቻይ አምላክ ዘፍ.17፡!
ኤልኦላም/ El Olam לא םלוע /፡- ዘላለማዊ አምላክ ዘፍ. 21፡33
ኤል ጊቦር/ El Gibbor לא רוביג /፡- ኃያል፣አሸናፊ እግዚአብሔር ኢሳ.9፡6-7
ኤል ኤልየን/ El Elyon לא ןוילע /፡- ታላቁ እግዚአብሔር ኢሳ.14፡18

እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ፥ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው፥ አሜን!ወደ ሮሜ ሰዎች 16:25-26